## ያለምኩት ሕልም*

ዛሬ ሌሊት ያለምኩት ሕልም እጅግ የሚደንቅ ነው
የዓለም ሕዝብ ተባብረን ጦርነትን ሻርነው...
ወንዱም ሴቱም ተሰብስበው ከታላቁ ቤት
ጦርነት ዳግመኛ እንዳይኖር ብለው ፈረሙት።

ፊርማው ሁሉ እንዳበቃ ሚልዩን ቅጂ ኣራብተው
ተመስገን ብለው ጸለዩ ግንባራቸውን ደፍተው...
ሕዝቡም ከውጭ እስክስታውን ያወርደው ነበር
በዘፈንና በደስታ ዕልልታም ጭምር።

ጦር- ጎራዴም ዳር ተጥሎ፣ ከንቱ ሆኖ ቀረ
ጦርነትም በዚያው ዕለት ሞቶ ተቀበረ።
ዛሬ ሌሊት ያለምኩት ሕልም እጅግ የሚደንቅ ነው
የዓለም ሕዝብ ተባብረን ጦርነትን ሻርነው...

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**

*ከኤድ ማክ-ከርዲ (Ed McCurdy) የተተረጐመ